# ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ቡና ላይ ለሚከፈለው ተጨማሪ እሴት ታክስ በዋስትና ስለሚያዝ ቫውቸር የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 19/1997

## 1. አውጪው ባለሥልጣን

የገቢዎች ሚኒስቴር ስለተጨማሪ እሴት ታክስ በወጣው ደንብ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 39 በተሰጠው ሥልጣን እና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በቁጥር አመ23/16/28/938 መጋቢት 22 ቀን 1995 ዓ.ም. በተሰጠው ውክልና መሠረት ይህን የቫውቸር አፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል::

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ቡና ላይ ለሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ በዋስትና ስለሚያዝ ቫውቸር የወጣ የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 19/1997" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## 3. ትርጓሜ

1. "ባለሥልጣን" ማለት የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ወይም እርሱ የወከለው የክልል/ከተማ አስተዳደር የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ነው::
2. "ሚኒስቴር" ማለት የገቢዎች ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር ነው::
3. "ቫውቸር" ማለት ቡና ላኪዎች ለቡና አቅራቢዎች በሚከፍሉት ተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን በዋስትና ለመክፈያነት የሚያገለግል ቼክ ነው::

## 4. የቫውቸር ቼክ አገልግሎት

1. የቡና ላኪነት ንግድ ፈቃድ ያላቸውና ቡና በጨረታ ማዕከል ግዢ የሚፈጽሙ ነጋዴዎች ለአቅራቢዎች ሊከፍሉት የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ በቫውቸር ቼክ ለመፈፀም ይችላሉ::
2. ቫውቸር ከተፈቀደለት ባለመብት በስተቀር ሊተላለፍ የማይችል ቼክ ነው::
3. ቡና ላኪዎች በጨረታ ማዕከል ከቡና አቅራቢዎች በሚገዙት ቡና ላይ ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ልክ በቫውቸር ቼኩ ላይ በፊደልና በአሃዝ በመሙላት ለቡና አቅራቢዎች መስጠት (መክፈል) አለባቸው::

338 348

5. **ቫውቸር ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ**

1. ማንኛውም የቫውቸር ቼክ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያመለክት ቡና ላኪ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ጥያቄውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል::
2. የቡና ላኪ ነጋዴው ለባለሥልጣኑ ሞልቶ ከሚያቀርበው የማመልከቻ ቅጽ ጋር አግባብ ባለው አካል የተሰጠውን የንግድ ሥራ ፈቃድና የዋና ንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል::

6. **የቫውቸር ቼክ አጠቃቀምን ስለመፍቀድ**

1. የባለሥልጣኑ መ/ቤት ከቡና ላኪ ነጋዴዎች የቀረበለትን ጥያቄ ከመረመረ በኋላ ለዚሁ ተግባር የሚውለውን ውል በማስፈረም ቫውቸሩን ለነጋዴው ይሰጣል::
2. ባለሥልጣኑ ለቡና ላኪ ነጋዴዎች የሰጠውን የቫውቸር ቼክ መጠን (ቁጥር) እንዲሁም የቫውቸሩ ተጠቃሚዎች በዋስትና ያስያዙትን መጠን በዋጋ ለይቶ በመመዝገብ በየወሩ ለሚኒስቴሩና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያቀርባል::

7. **ቫውቸር ቼክ የተሰጠበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሣብ ስለማወራረድ**

1. የቫውቸር ሥርዓቱ ተጠቃሚ የሆነ ቡና ላኪ ቫውቸር በመስጠት በጨረታ ማዕከል የገዛውን ቡና በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7(2) መሠረት ወደ ውጭ መላኩን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ዋናውንና ኮፒውን ለባለሥልጣኑ በማቅረብ የቫውቸር ቼኩን ሂሣብ የማወራረድ ኃላፊነት አለበት::
2. የቀረቡትም ማስረጃዎች በባለሥልጣኑ ከተመረመሩና ሊወራረድ የሚገባው የታክስ ስሌትም ከተከናወነ በኋላ የቫውቸር ተጠቃሚው ያስያዘው ቫውቸር ቼክ በባለሥልጣኑ እንዲወራረድ ይደረጋል፣ የተወራረደውንም የቫውቸር ቼክ "የተወራረደ" የሚል ማህተም ተደርጐበት በባለሥልጣኑ በጥንቃቄ እንዲቀመጥ ይደረጋል:: የተወራረደውንም የቫውቸር መጠን ዝርዝር የሚያሳይ ሪፖርት ባለሥልጣኑ በየሶስት ወሩ ለሚኒስቴሩ እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ይልካል::
3. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4/3/ መሠረት በቫውቸር ቼክ ዋስትና ተሰጥቶ የተገዛ ቡና ግዥው ከተፈፀመበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ

ወደ ውጭ አገር ካልተላከ ወይም በዚህ መመሪያ መሠረት የጊዜ ገደቡ ተራዝሞ ከሆነ በተራዘመው ጊዜ ውስጥም ቡናው ወደ ውጭ ለመላኩ ማስረጃዎች ለባለሥልጣኑ ቀርቦ ቫውቸር ቼኩ እንዲወራረድ ካልተጠየቀ በስተቀር ዋስትናውን ያስያዘው ሰው ወይም ድርጅት በጨረታ ማዕከል በገዛው ቡና ላይ ሊከፍል ሲገባ የታለፈውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ከነወለዱ ይከፍላል::

4. የቫውቸር ተጠቃሚ የሆነ ቡና ላኪ ነጋዴ ወይም ድርጅት የቡና ላኪነት ሥራውን በማቋረጡ ምክንያት ቫውቸር ቼኩን የመለሰ እንደሆነ በተመለሰው ቫውቸር ላይ "ያልተሠራበት" የሚል ማህተም ተደርጐበት በባለሥልጣኑ በጥንቃቄ እንዲቀመጥ ይደረጋል::

8. **ቫውቸር ለማወራረድ የሚቀርቡ ማስረጃዎች**

የቫውቸር ቼክ ተጠቃሚዎች በጨረታ ማዕከል በገዙት ቡና ላይ ለሚከፈል ተጨማሪ እሴት ታክስ ያስያዙትን ቫውቸር ቼክ ለማወራረድ ጥያቄአቸውን ለባለሥልጣኑ መ/ቤት በሚያቀርቡበት ጊዜ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ዋናውን እና ኮፒውን አሟልተው ማቅረብ አለባቸው::

1. ወደ ውጭ የተላከውን ቡና መጠን እና ዋጋውን፣ ለውጭ ገበያ ሊቀርብ ባለመቻሉ በአገር ውስጥ የተሸጠውን፣ በዝግጅት ሂደት ከጥቅም ውጭ የሆነውን የሚያሳይ በላኪው የተዘጋጀና በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ማረጋገጫ የተሰጠበት መግለጫ፣
2. በጨረታ ማዕከል ለውጭ ገበያ እንዲውል የተገዛው ቡና ለውጭ ገበያ መላኩን የሚያረጋግጡ፣
   - የጉምሩክ ዲክላራሲዮን
   - ደረሰኝ (Commercial Invoice)
   - የማስጫኛ ሠነድ (Bill of lading/Airway bill)
   - የባንክ ፈቃድ
   - ቡናው ከተላከ ከ3 ወር በላይ ከሆነ የተገኘውን የውጭ ምንዛሪ የሚያሳይ የባንክ ደረሰኝ (Bank Credit Advice)

   ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል::

9. **በዝግጅት ሂደት ስለሚባክን ቡና**

1. ወደውጭ አገር የሚላክ ቡናን በማዘጋጀት ሂደት የባከነው ቡና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8/1/ በተመለከተው መሠረት ላኪው ባዘጋጀው መግለጫ ውስጥ ያለመካተቱ ሲረጋገጥ ከ2% /ሁለት በመቶ/ የማይበልጥ የብክነት

347

መጠን ጨምሮ ማስላት ይቻላል:: ሆኖም የታጠበ ቡና በሚሆንበት ጊዜ የብክነት መጠኑ ከ0.8%/ዜሮ ነጥብ ስምንት በመቶ/ ሊበልጥ አይችልም::

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም እንደቡናው ባህሪ የብክነት መጠን መጨመር ሲያስፈልግ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ጉዳዩን በጥንቃቄ መርምሮ በልዩ ሁኔታ ተጨማሪ የብክነት መጠን ሊፈቅድ ይችላል::

## 10. <u>የጊዜ ገደብ ስለማራዘም</u>

1. ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ በጨረታ ማዕከል የተገዛ ቡና ግገርው ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደውጭ ካልተላከ ባለሥልጣኑ ይህ የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል::
2. ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 በተመለከተው መሠረት ባለሥልጣኑ የጊዜ ገደቡን ለተጨማሪ አንድ ዓመት ሊያራዝም የሚችለው፤
   ሀ. የቡና ላኪው ድርጅት ለቡናው ዝግጅት የሚጠቀምበት ማሽን በመሠበሩ ወይም በሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ምክንያት ድርጅቱ ከአንድ ወር ላላነሰ ጊዜ ሥራ ማቆሙ፣ ወይም
   ለ. በዓለም ገበያ የቡና ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በመውደቁ ምክንያት ቡናውን መላክ ያልተቻለ ሲሆን፣
   ሐ. ቡናውን ለመግዛት የተዋዋለው የውጭ ድርጅት ውሉን ማፍረሱ ሲረጋገጥና ሌላ ገበያ ለማግኘት ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም
   መ. በፍትሐብሔር ሕግ በተደነገገው መሠረት ቡናውን ለውጪ ገበያ ለመላክ የማያስችል ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም፣ ይሆናል::

## 11. <u>የቡና አቅራቢዎች ግዴታ</u>

1. የቡና አቅራቢዎች በጨረታ ማዕከል ለቡና ላኪዎች በሚሸጡት ቡና ላይ ተከፋይ ለሆነው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመጣጣኙን ዋጋ የያዘ ቫውቸር ቼክ መቀበል አለባቸው::
2. ቡና አቅራቢዎች ለተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ በዋስትናነት ለተቀበሉት ቫውቸር የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ይሰጣሉ::
3. ከቡና ላኪዎች የተቀበሉትን ቫውቸር በየወሩ ለባለሥልጣኑ ገቢ ማድረግ አለባቸው::

12. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ ሲሰራበት በነበረው የቫውቸር ሥርዓት ለቡና ላኪዎች የተሠራጨው ቫውቸር ይህ መመሪያ ፀንቶ ሥራ ላይ እንዲውል ከተደረገበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋለውና ያልዋለው ተለይቶ ለባለሥልጣኑ መ/ቤት ተመላሽ ይደረጋል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ከቡና ላኪዎች ተመላሽ የተደረገውን ያልተሠራባቸውን ቫውቸር ተረክቦ በመመዝገብ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡
3. የተሠራባቸው ቫውቸሮች ሥራ ላይ በነበረው የቫውቸር ሥርዓት መመሪያ መሠረት እንዲወራረዱ ይደረጋል፡፡

13. <u>ኃላፊነት</u>

ሚኒስቴሩ የቫውቸር ቼክን የማሳተም ሙሉ ሥልጣንና ኃላፊነት ያለው ሲሆን ያሳተማቸውን ቫውቸሮችም ለባለሥልጣኑ በሠነድ ያስረክባል፡፡

14. <u>የተሻረ መመሪያ</u>

ለውጭ ገበያ ለሚውል ቡና አጠቃቀም ግንቦት 8 ቀን 1995 የወጣው የቫውቸር አፈፃፀም መመሪያ ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

15. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከሕዳር 13 ቀን 1997 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ---------- ቀን 1997 ዓ.ም.

**ጌታቸው በላይ**

**የገቢዎች ሚኒስትር**